# ያርበኞች ግንባር የዉጭ ኮሚቴ አሰራርና ዉዝግብ።

**በጥቁር ጫካ።** Chakatikur4@gmail.com

ሻብያ ያርበኞች ግንባር ሰራዊትን በመዳፉ ካስገባ በኋላ የዉጭ ኮሚቴዉን አጠናክራለሁ በማለት ከዉጭ ከሚመጡት ኢትዮጵያዉያን ጋር ሽርጉድ ማለት ጀመረ፣ ከዉጭ ከሚመጡት አባላት የመጨረሻ የታሪክ ዝቃጭ የሆነዉን ሰለሞን ከዳልኝ (ተካልኝ) እንተወዉና አሁን ስላሉት እናዉራ።

ከዉጭ ስራየ ብለዉ ከሚመላለሱት መካከል እነ አቶ ደምስ በለጠ፣ አቶ ኤልያስ ክፍሌ፣ አቶ ስለሽ ጥላሁን, አቶ መልኬ መንግስቴ፣ አቶ ዘዉዳለም፣ እንዲሁም ሌሎችም ይጠቀሳሉ፣
እነዚህ ሰወች ኤርትራ ሲመጡ ሁሉን ነገር የሚነጋገሩት ካርበኞች ግንባር አመራሮች ጋር ሳይሆን ከሻብያ ባለስልጣኖች ጋር ነዉ፣ ሁላችንም ስለ ስራ እቅድ መመሪያ የምንቀበለዉ ከሻብያ ነዉ፣ ለስሙ ቢሮ አለ፣ ግን ሊቀመንበር ተብየዉ አቶ ማአዛዉና ሌሎችም ለሳምፕል የተቀመጡ እንጅ, ምንም ነገር የመወሰንም ሆነ የማስፈፀም መብትም አቅምም የላቸዉም።
መአዛዉ አንዳንድ ነገር ስንጠይቀዉ, ቆይ ኮ/ል ፍፁምን አነጋግሬ እነግራችኋለሁ ነዉ መልሱ፣ ወይም፣ ኮ/ል ፍፁምን ወይም ወዲ ምስግናን ጠይቁት ነዉ የሚለዉ።
ወዲ ምስግና የኤርትራ የደህንነት ባለሰልጣን ነዉ፣ ኮ/ል ፍፁምን አብዛኛዎቻችሁ ታዉቁታላችሁ፡ሁሉም የተቃዋሚ አባላት ከዉጭ የምንሄድ ሁሉ ለሰራዊቱ ወይም ለአርበኞች አመራር ሳይሆን, ለነሱ ነዉ ደፋቀና እያልን የምንነጋገረዉ, እንጅ ሰራዊቱ ትዝም አይለን፡ አንዳንዶች ግንባር እየሄዱ ሰራዊቱን ፎቶ ና ቪዲዮ ቀርጾ መመለስ የተለመደ ነዉ፡ ወደዉጭ ሲመለሱ ብር መሰብሰቢያና ቅስቀሳ ማካሄጃ መሆኑ ነዉ።
ድሮ የዉጭ አመራር የሚባል የለም ነበር፣ ሁሉም በያለበት አገር ሆኖ ለወዲ ምስግና ወይም ለኮ/ል ፍፁም ስልክ በመደወል ስብሰባ ጠርቸ ገንዘብ ልሰበስብ ስለሆነ, የዉክልና ደብዳቤ ላኩልኝ ብሎ ሲደዉል, ወዲያዉ እነ ወዲ ምስግና በዛ አገር ያርበኞች ተወካይ ነዉ ብለዉ የዉክልና ደብዳቤ ይልኩለታል፣ ሰዉዬዉም እንደምንም ብሎ ከቅርብ ጓደኞቹም ከዛም ከዚም ብሎ የተወሰነ ገንዘብ ይሰበስብና የተወሰነዉን ወደ አስመራ ለነ ኮ/ል ፍፁምና ወዲ ምስግና ይልክና የቀረዉን ወደኪሱ ማድረግ የተለመደ ነበር።
እዛዉ አገር ሌላዉ የሱ ጓደኛ ይነሳና እንዴት ለሱ የዉክልና ደብዳቤ ይላክለታል, እኔስ ከሱ በምን አንሳለሁ ይልና እሱም የዉክልና ደብዳቤ እንዲላክለት አስመራ ይደዉላል፣ ኢትዮጵያዉያን እርስ በርሳቸዉ እንዲጋጩ የሚፈልጉት ሻብያዎች, እንዲያዉም መነሻ ሰበብ ከኛ ከተነሳማ ደስታቸዉ ነዉ፣ ስለዚህ ወዲያዉ ፅፈዉ ይልኩለታል።
እሱም እኔነኝ ተወካይ በማለት ዉስጥ ለዉስጥ ቅስቀሳና ገንዘብ መዋጮ መሰባሰብ ይጀምራል። እሱም ከሰበሰበዉ ገንዘብ የተወሰነዉን ወደ አስመራ ልኮ የተወሰነዉን ወደ ኪሱ ያደርጋል።
እዚህ ላይ ነዉ እንግዲህ ላንድ አላማ ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት ተሰለፍን የሚሉት ያንድ አገር ልጆች በሻብያ ቆስቋሽነት እርስ በርስ ዉዝግብ ዉስጥ የሚገቡት።
አንደኛዉ ተነስቶ, ለምን ለሱም ደብዳቤ ላካችሁ, ብሎ በኩርፊያ ወደ አስመራ ይደዉላል፡ አስመራወች ታዲያ ሰዉ ማባበል መች ያቅታቸዋል፡ እንኳን የኛን ቡድን መንፈሰ ደካማና ሞራለቢስ የሆነዉን በአድር ባይነታችን በደንብ ያወቁንን ቀርቶ, ለእዉነጠኛ ፖለቲካ የቀረባቸፊዉንም ጠንካራ ሰዉ በፀባይ አግባብቶ መሾንት ተክነዉበታል።
የሻብያ ባለስልጣኖች ሲዎዱህም ሲጠሉህም አንድ አይነት አቀራረብ ነዉ ያላቸዉ፡ ፊታቸዉ አይቀየርም፣ እነሱን የሚፈታተናቸዉንና ለእዉነተኛና ለጋራጥቅም የሚቆመዉን አይወዱትም፡ እንደሚጠሉትም አይታወቅባቸዉም፡ ግን ቀስ ብለዉ ግዜ ወስደዉ ነዉ እያሹ የሚጎዱት፡ ለዚህ ምሳሌ ደግሞ እነ ኮ/ል ታደሰ, አቶ ዮሴፍ, ሻ/ል ዘዉዱ ጄ/ል ከማል ጀ/ል ሀይሉ, አቶ ዮናታን, ኮ/ል አበበ ሌሎችም ብዙ አሉ፣ ኢትዬጵያዊነት አቋም ስለያዙና ያድር ባይነት ፀባይ ስለሌላቸዉ እንዲሁም ጣልቃ አትግቡብን ስላሉ, ሻብያ እያሸ እያሰቃያቸዉ ነዉ።
ታዲያ ሁላችንም ለምን ከኔ ሌላ እዚህ አገር ሰዉ ተወከለ ብለን ስንደዉል, በጣም ይቅርታ በስህተት ነዉ እኛ ሳናዉቅ ነዉ, ባጋጣሚ እነ መአዛዉና እነ ኑርጀባ ተሳስተዉ ነዉ ብለዉ ነገሩን ዘወር ያደርጉታል፣ እግረ መንገዳቸዉን እነ መአዛዉ ስራ እንደማይችሉና ሻብያም ጣልቃ የሚገባዉ ሊያግዛቸዉ እንደሆነ ለማሳመኛ መሆኑ ነዉ።
እነ ኑርጀባና መአዛዉ ችሎታ ቢኖራቸዉም ከነ ኮ/ል ፍፁም ትዛዝ ዉጭ አንድም ነገር ማድረግ እንደማይችሉ የምናዉቅ አይመስላቸዉም።
አንዳንዴ ደግሞ ከቻላችሁ ዝምብላችሁ ተስማምታችሁ ስሩ፡ ካልተስማማችሁ ከተወሰነ ግዜ በኋላ የእያንዳንዳቸሁን እንቅስቃሴ አይተን ጥሩ ስራ የሰራዉን የድረጅቱ ተወካይ መሆኑን ከደብዳቤም አልፎ በሚዲያምና በዌብሳይትም እንነግርለታለን ብለዉ ያግባቡታል፡ ታዲያ ይህን ስንባል ያን ሹመት ለማግኘት የባዶ ዉሸት ፕሮፓጋናዳ ለቅርብ ጓደኞቻችን እየቀደድን ገንዘብ ሰብስበን ትንሽ ቦድሰን መላክ ነዉ፡ ከመላክም አልፈን፣ ለሻብያ ባለስልጣኖች, የራሳችን ወንድሞች ያደረጉትን ያላደረጉትን ሁሉ እየወሰድን ወሬ ማቀበልም የተለመደ ሆኗል፡ አንዱ ስላንዱ ስም ማጥፋትና, ከእድሜያችንና ከተሰለፍንበት አላማ ጋር የማይሄድ አስነዋሪ አሜት የተለመደ ሆኗል።
ያርበኞች ግንባር ድሮ እንደ ድርጅት ስርአት ያለዉ የዉጭ ኮሚቴ የሚባል ነገር አልነበረዉም፡ እነ ልኡል ቀስቅስ እዉነት መስሏቸዉ ሊዋጉና ሊያዋጉ ወደ ኤርትራ ሲገቡ የጠበቃቸዉ ግን በኤርትራዉያን የሚመራ, ፖለቲካዊና አገራዊ ራይ የለላቸዉ ሰወች የድርጅቱ መሪ ተብለዉ ሲጠብቃቸዉ በጥልቀት ሞራላቸዉ ተነካ።

ወዲያዉ መታገልም ማታገልም እንደማይችሉና ድርጅቱ ብዙነገሮች መሟላት ያለባቸዉ ነገሮች መኖራቸዉን እንደተረዱ, ከሻብያ ባለስልጣናት ጋር ተለሳልሰዉና ተግባብተዉ እራሳቸዉን ለማዉጣት ወደ ጀርመን አቀኑ። ታዲያ እግረ መንገዳቸዉን የዉጭ ኮሚቴ መጠናከርና ስራዉን መስራት እንዳለባቸዉ, እነ ጄ/ል ተክላይንና ኮ/ል ፍፁምን በማግባባት የዉጭ ኮሚቴ ሙሉ ዉክልና አፅፈዉ ነዉ የሄዱት፡ እንደሄዱ ያቅማቸዉን ለመንቀሳቀስ ሞክረዋል ትንሽ ነፍስ እንዲዘራበትም አድርገዋል።

ታዲያ ትንሽ ሳይቆይ, ከሌሎች ጋር መናቆር ጀመሩ፡ እነ ስለሽ ጥላሁን እኛ ከነሱ ቀደምት እያለን ለምን ለነሱ የዉጭ አመራር ተሰጣቸዉ በሚል ዉዝግብ አንስተዉ ዱላቀረሽ ጥል ዉስጥ ገቡና ከሁለት ተከፈሉ፡ የነ ስለሽ ቡድን ባንድ በኩል, የነ ልኡል ቡድን ባንድ በኩል ንክሻ ጀመሩ፡ ይህ ጥል ወደ ጎጥ ሄዶ ነበር, የነ ልኡል ግሩፕ አብዛኛዉ ማለት ይቻላል ጎንደሬዎች ይበዙ ነበር።

**ያርበኞች ጉባኤ።**ያርበኞች ግንባር ባለፈዉ በ2009 መለስተኛ ጉባኤ አካሂዶ ብዙ ተወርቶለታል፣ ትንሽ ቆየት ብሎም ጠቅላላ ጉባኤ ተካሄደ።
ወገኖቸ ታዲያ ይህ ጉባኤ እንዴት እንደሚካሄድና ጉባኤዉን ማን እንደሚመራዉ ታዉቃላችሁ?

ባሁኑ ሰአት ያርበኞች ግንባር ስብሰባም ሆነ ዋና ድርጅታዊ ጉባኤ የሚያካሄደዉ እንዲህ ነዉ፣
ከመጀመሪያዉ የስብሰባዉን አጀንዳ የሚያዘጋጁት እነ ወዲ ምስግና እና ኮ/ል ፍፁም ናቸዉ፣ ቀላል ስብሰባ ሲሆን ኮ/ል ፍፁም ወይ ወዲ ምስግና ይመሩታል፡ አቶ መአዛዉና አቶ ኑርጀባ ለይስሙላ አብረዉ ይቀመጣሉ። ከበድ ያለ ወይም ጠቅላላ ድርጅታዊ ጉባኤ ሲሆን, ጄ/ል ተክላይ እና ወዲ ምስግና ይመሩታል፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ሁሉም ከዉጭ የመጣ ይሰበሰባል፡ የሚገርመዉ ስብሰባዉ የእኛ የኢትዮጵያዉያን ሆኖ ሳለ የሻብያ ባለስልጣኖች ስብሰባዉን ሲመሩት ማንም የኛ ሰዉ ትንፍሽ ብሎ አያዉቅም፡ ከዉጭ ከመጣነዉ በእድሜም በስራ ልምድም ከሁላችን የሚሻሉት የሶስት መንግስት ልምድ ያላቸዉ የኛ ሰወች ምንም አስተያየትም ተቃዉሞም ትንፍሽ አይሉ።

የኤርትራ መንግስትም ሻብያና ወያኔ ሱዳን ተጠግተዉ ለረጅም ግዜ ሲታገሉ, የሱዳን መንግስትም ሆነ ሌሎች የሚረዷቸዉ መንግስታት በነሱላይ አድርገዉባቸዉ የማያዉቁትን በኛላይ ማድረጋቸዉ ትልቅ ንቀትና ታሪካዊ ስህተት ነዉ።

ሻብያ በኢትዮጵያ ላይ ያላለቀ አጀንዳ ስላላቸዉ እሽ የሚል አድር ባይ እስካገኙ ድረስ ሁሉን ነገር ከማድረግ ወደኋላ አይሉም፡ የምንገርመዉ እኛ እራሳችን ዝምብለን መመራታችን ነዉ።
ኤርትራ ያሉትን ያርበኞች አመራር በዚህ ነገር ላይ ምንም ተጠያቂ አላደርጋቸዉም፡ ምክንያቱም ሁሉም እዛ አመራር ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ ሰወች, ድርጅት ማለት ምን ማለት እንደሆነ አያዉቁም፡ ትግል ማለት ተኩስ መተኮስና መግደል መጋደል ብቻ አድርገዉ የሚያስቡ ናቸዉ እንጅ, የትግል ዋና መሰረቱ, መጀመሪያ ድርጅታዊ አቋምና ስርአት ያለዉ መመሪያና መተዳደሪያ ደንብ መኖርና መከበር እንደሆነ አያዉቁም።
ከነዛ ዉስጥ,የአርበኞች ግንባር ሊቀመንበር ተብየዉ አቶ መአዛዉ ማንበብና መፃፍ የማያዉቅ በኮ/ል ፍፁም የሚታዘዝ ነዉ፡ አንዳንድ ያርበኞች ቢሮ ዉስጥ የሚፃፉ ነገሮች ሲኖሩ, ኮ/ል ፍፁም ለኑርጀባ እንዲህ እንዲህ አድርገህ ፃፍና መአዛዉ ይፈርምበት ይባላል፣ ኑርጀባ በትምህርት ከሁሉም ስለሚሻል ይፅፍና መአዛዉን ፈርም ይለዋል፡ ታዲያ አቶ መአዛዉ ምን እንደተፃፈ ሳያነብ, የፊርማ ቦታዉን ብቻ አይቶ መፈረም ነዉ ስራዉ፡ መአዛዉ ብዙ ግዜ ቁጭ ብለን ስንወያይ በግድ ካላዋራነዉ መናገርም አይፈልግ ቢናገርም አይችል እነ ፍፁም እሽ አዎ እያለ የሚታዘዝ ስላገኙ መጫዎቻቸዉ ሆኗል።

አቶ ኑርጀባ የድርጅቱ የፖለቲካ ሀላፊ ተብየዉ፣ ትንሽ ከሁሉም በትምህርትና በመናገር ካሉት ይሻላል፣ ግን በጣም ፈሪ ነዉ፡ እነ ኮ/ል ፍፁምና ወዲ ምስግና አድርግ ወይም ተናገር ካላሉት አንድም ነገር ትንፍሽ አይልም አንድም ነገርም ስራ አይሰራም፡ ጥሩ ታዛዣቸዉ ነዉ፡
ኑር ጀባ, እነ ኮ/ል ፍፁም በጠንካራ ያርበኞች ግንባር ሰወች ላይ የሰሩትን የድብቅና የግልፅ ጭፍጨፋ ስለሚያዉቅ በጣም ተጠንቅቆ ነዉ የሚኖረዉ፡
ወደ ዉጭ እንልክህለን ብለዉ ቃል ስለገቡለት ያን እንኳ እንዳይሰርዙበት ፀጥ ለጥ ብሎ ነዉ የሚታዘዛቸዉ፡
እነ መንግስቱም ከነ ኑርጀባ ብዙም አይለዩም፡ ባጠቃላይ ሁሉም የሚጨቃጨቁት የኪስ ገንዘባቸዉ ጎደል ስትል ነዉ፡ ሻብያ ደግሞ ገንዘብ አጠፉህ በላህ ብሎ አይቀየምህም፡ እንዲያዉም ካጠገቡ አድርጎ ባድርባይነት ሊጠቀምባቸዉ የሚሰበስባቸዉን ሰወች፣ ካሁን በፊት አይተዉት የማያዉቁት ኑሮና ጥቅም ማስለመድ ባህሪያቸዉ ነዉ።
ድሮ አግኝቶት የማያዉቀዉን ገንዘብ ሲቆጥርና የምቾት ኑሮ መኖር ሲጀምር, ፀጥ ለጥ ብሎ ነዉ የሚገዛ፣ ሻብያም አስመራ ያሉትን ሁሉንም አመራር ተብየወች ናቅፋ እንደልብ ስለሚያፈስላቸዉ, ከሀገሬዉ ሰዉ በበለጠ በደንብ ይዝናናሉ፡ ያገሬዉ ሰዉ ሲዝናና ሻብያን በመፍራት ተሸማቆ ነዉ፡ ትንሽ የባህሪ ለዉጥ ከታየባቸዉ ጥቅሙ ይቀርብናል ብለዉ ስለሚፈሩ በደንብ ታዛዥ ይሆናሉ፡ ይህ ነዉ እንግዲህ በወገን ደምና በሀገር መነገድ።

ታዲያ እንግዲህ፡ ከዉጭ የሚመጡት በሙሉ፡ ሻብያ ነገሩን ሁሉ እንደዚህ እያበላሸዉ ሲሄድ ዝም ብለዉ ማየት አልነበረባቸዉም፡የማስተካከል አቅሙም ተሰሚነቱም ነበራቸዉ, የማይስተካከል ከሆነ ለወገናቸዉ ነግረዉ በሌላ ስልት ትግሉ እንዲቀጥል ማድረግ ነበረባቸዉ፡ ስለዚህ ለዚህ ሁሉ እያወቁ ዝም ማለታቸዉ ስህተት ነዉ ወደሚለዉና ጥፋተኛ ናቸዉ ወደሚለዉ ይወስደናል።

ከዉጭ የምንመጣ ኮሚቴ ተብዬዎች በሙሉ ትልቅ ጥፋተኞች ነን፡ ለወያኔ አገዛዛ የተመቸነዉ እኛ እንደሆንን ሁሉ ሻብያም ያርበኞች ግንባርን እንደፈለገ እያደረገ እንዲያዳክመዉ የተመቸነዉና ያገዝነዉ ካዉሮፓና ካሜሪካ የምንመጣ ሰወች ነን።

አስመራ በገባን ቁጥር ያርበኞች መሪ ከተባሉት ጋር መነጋገርና መወያየት ሲገባን የምንወያየዉ ከሻብያ ባለስልጣኖች ጋር መሆኑ ዉርደት ነዉ፡ እንደነ መአዛዉ ያሉ ሰወች ወርደዉ በችሎታቸዉ ተመድበዉ ይታገሉ፡ በምትካቸዉ ቁርጠኛና የፖለቲካ ችሎታ ያላቸዉ ይመረጡ ብለን መናገር ሲገባን እየሄድን ከስራቸዉ እናሸረጉዳለን።

ጉባኤ ሲደረግ እነመአዛዉና ኑርጀባ ስብሰባዉን መምራት ካልቻሉ, ሌሎች ከድርጅቱ ችሎታ ያላቸዉ ስብሰባዉን ይምሩት ብለን የመናገር ሞራልና ድፍረት እየተሳነን, ዝምብለን በሻብያ አመራሮች ተሰብስበን ቀደም ብለዉ ያሰራጩትን መመሪያና እቅድ  አፅድቀን እንበተናለን፡

ስለሰራዊቱ ሁኔታ ምንም አንጠይቅም፡ ስለሰራዊቱ እነሱ የነገሩንን የተጋነነ የባዶ ወሬ መስማት ብቻ ነዉ እንጅ ሄደን እንጎብኝ አንልም፡ የሰራዊቱ ንቃትና ሞራል እንዴት ነዉ, ምን ችግርስ አለበት ደስ እንዲለዉ ሄደን እንጎብኘዉና እናነጋግረዉ ብሎ መጠየቅ የለም፡ አንዳንዶች ሲጠይቁ የሚሰጣቸዉ መልስ ጥሩ እንደሆነ, ትልቅ ዘመቻ እያካሄደ እንደሆነ ይነግሩናል፡ ወደግንባር ሄደን እንጎብኝ ብሎ የሚያስብ በጣም ትቂት ነዉ፣ እሱም ለገንዘብ መሰብሰቢያ ፎቶና ቪዲዮ ለመቅረፅ የፈለገ ነዉ እንጅ, የሰራዊቱን ኑሮና ሞራል ወይም ምን ችግር እንዳለበት ለመጠየቅና ለማወያየት አይደለም።

የሻብያ ባለስልጣኖች እነ ኮ/ል ፍፁም በድብቅ ያስገደሉዋቸዉን ቁርጠኛ ወንድሞቻችንን **እነ ተስፋዬን, እነ ሽባባዉን,** እንዲሁም ሌሎች ብዙ አሉ, የት ገቡ የት ተሰወሩ ብሎ ደፍሮ የሚጠይቅ የለም፡ የነዚህን ንፁህ ወንድሞቻችን በስዉር መገደል ያልሰማ የለም፣ ግን ማንም የት ገቡ ብሎ በስብሰባም በተናጠልም አንጠይቅም፣ የሞቱት ይቅርና ያሉትንም እነኮ/ል ታደሰና አቶ ዮሴፍን ለምን ከድርጅቱ ተባረሩ ታገዱ ብሎ የሚጠይቅ ሞራል ያለዉ የለም።

በተለይ ዉድ ወንድሞቻችን, ተስፋዬና-ሽባባዉን, እንዲሁም በርካቶችን, አቶ መስከረምና ኮ/ል ፍፁም እንዳስገደሏቸዉ, አቶ መልኬ መንግስቴ እያወቀ ዝም በማለቱ ተጠያቂ ነዉ፡ ከድሮ ጀምሮ ሁሉንም ስለሚያዉቅ, የት ገቡ ለምን ሞቱ ብሎ ማፋጠጥ መጠየቅና ለህዝብ ማሳወቅ ግዴታዉ ነበር፡ ስለኮ/ል ታደሰና ስለ አቶ ዮሴፍም ከድርጅቱ በግፍ ተባረዉ ዮሴፍ ተሰኔ በረሀ በእስር ተሰቃይቶ ከተፈታ በሗላ, ያለ ዘመድ ብቻዉን የቁም እስርኛ ሆኖ በረሀ ሲጣል, እነ አቶ መልኬ መንግስቴና አቶ ዘዉዳለም በደንብ ሰምተዉ እያወቁ, ከተባረሩ ከወደቁ ምን ያደርጉልናል ብለዉ ከአዲሶቹ ጋር ሽርጉድ ማለት የትግል መሪና የፖለቲከኛ ስነምግባር አደለም።

የትግል አመራር ማለት አዲስ ተተክቶና ያለዉም ከልቡ በሞራል እንዲታገል, የተሰዉትን መዘከርና የተጎዱትን መንከባከብ እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡ እነዛን ከረሳናቸዉና ከጣልናቸዉማ, የቀረዉም ነገም በኔ እያለ በሞራልና ከልቡ አይታገልም።

ሻብያና ወያኔ በረሀ እያሉ ሰራዊት እንደጉድ የጎረፈላቸዉ በዚህ የተጎዳን እንክብካቤ ባህላቸዉ ነዉ።

አቶ ዮሴፍና ኮ/ል ታደሰ ድርጅቱን ለማስተዋወቅ አሜሪካ በሄዱበት ወቅት እነ አቶ ዘዉዳለምና ሌሎች ጓደኞቻቸዉ አቶ ዮሴፍን እንዴት አክብረዉ ያስተናግዱት እንደነበር የቅርብ ታሪክ ነዉ፡ ወደ አስመራ ሲመጡም ለነ ኮ/ል ታደሰና ለዮሴፍ እንዴት ደፋ ቀና እያሉ እንደሚያሽቃብጡ የትናንት ያልበረደ ትኩስ ታሪክ ነዉ፡

ሻምበል ዘዉዱ አርበኛዉን ተቀላቅሎ እንደተሾመ, እነ አቶ መልኬና አቶ ዘዉዳለም እንዲሁም ሌሎች የነሱ ጓደኞች ያገራቸዉ ልጅ ጎንደሬ ስለሆነ, እጅግ በጣም ነበር የሚንከባከቡትና ደፋቀና የሚሉለት፡ ሻ/ል ዘዉዱ ግን, ለኢትዮጵያዊነትና ለእዉነት ለቆሙት እንጅ, ያገር ልጅ የሚባል ላረጀ ላፈጀ ጎጠኝነት አስተሳሰብ, ቦታ አይሰጥም ነበር፡

ወደ አስመራ በሚሄዱበት ግዜ, አብዛኛዉ ሻንጣቸዉ ለሻ/ል ዘዉዱና ለነኮ/ል ፍፁምና ወዲ ምስግና ፀሀፊወች ልብስና ስጦታ ሻንጣቸዉ የተሞላ ነበር፡ ታዲያ በ2009 እንደተለመደዉ እነ አቶ መልኬና አቶ ዘዉዳለም አስመራ ሲሄዱ ሻ/ል ዘዉዱ ከበረሀ ወደ አስመራ ለአጭር ስራ በሚል ምክንያት መጥቶ ወይ ስራ አያሰሩት ወይ አያባርሩት ኮ/ል ፍፁምና መአዛዉ ዝም ብለዉ ለይስሙላ ቢሮ አስቀምጠዉ ያበሳጩታል፡ ነገሩን በሹክሹክታ የሰሙት የነ አቶ መልኬ, ሻ/ል ዘዉዱን መቅረብና ሰላም ማለት እንኳ አልፈለጉም እራቁት።

ይህ ከዉጭ የሚመጣ ግሩፕ አንድ አስመራ ያለ ያርበኞች አባል ከነ ኮ/ል ፍፁም ጋር ከተጣላ ሁሉም ስለሚፈራ ይርቁታል፡ ከሱ ጋር ከታየን ይቀየሙናል ብለዉ ያስባሉ፡ ኤርትራ ያሉ አባላትማ, የተገለለን አባል እንኳን አብሮ ሻይ ቡና ማለት ቀርቶ መንገድ ላይ ፊት ለፊት ሲተያዩ ቶሎ መንገድ መቀየር እንደመመሪያ ሆኖ ይተገበራል፣ ሁሉም ያንድ አገር ልጅ ሆነዉ ላንድ አላማ ወደሰዉ አገር ተሰደዉ, በልባቸዉ እየተዋደዱና እየተነፋፈቁ, ሻብያን በመፍራት ለጎሪጥ መተያትና ተሸማቆ መኖር ባህል ሆኗል።

ሻ/ል ዘዉዱ እንደሌሎች ለግል ጥቅሙ ቢያስብ ኖሮ ሻብያ የሚለዉን እሺ እያለ በሰላም በድሎት ይኖር ነበር፣ እንደሌሎችም ወደ ዉጭ ይልኩት ነበር።

ሻ/ል ዘዉዱ ግን ለሀገሩ ለወገኑ በተለይ ያርበኛዉ ሰራዊት ለምን ይበደላል ለምን በሻብያ ይታዘዛል, ችሎታ ያላቸዉ ሰወችስ ለምን ተመርጠዉ አይመሩትም, የሚል አቋም ስለያዘ, በሻብያ ጥርስ ዉስጥ ገብቶ አስመራ ብቻዉን ሲንከራተት አንድም ለምን ተባረረ ለምን እሱባለበት ችግሩ አይነገረንም እሱም ችግሩንና ልዩነቱን

ይናገር ብሎ ለመጠየቅ አገራዊና ወገናዊ ሞራል አነሳስቶት የጠየቀ የለም፡ ይባስ ብሎ ድሮ እንደዚያ ስናጎበድድለት የነበርነዉ ስናየዉም መሸሽ ጀመርን ያሳዝናል።

ኮ/ል ታደሰ, ሻ/ል ዘዉዱና ዮሴፍ, ትሰሙኛላችሁ? ፅናቱን ይስጣችሁ። ለሆዳሞችና ለክፉዎች ግዜ እንዳላቸዉ፡ ለሀቀኞችም ግዜ አላቸዉ፡ ግን ክፉዎችና ሆዳሞች እረዘም ያለ ግዜና እድል ያጋጥማቸዋል። የሀቀኞችና ቅኑዎች እድልና ግዜ ግን አጭር ናት፡ ያችንም ቢሆን እግዚአብሄር ያምጣላችሁ። ስትመጣላችሁም ተጠቀሙባት፣ ሰማችሁኝ? አንድ ሀቅ አለ፡ በአለምላይ ክፉዎችና ሆዳም ተንኮለኞች ከሀቀኛች እጅግ ይበዛሉ፡ ለዚህ ነዉ አለም የሚበጠበጠዉ፡ እንደ ሀይማኖታችንም ሆነ እንደ ሳይንስ, ብናስብ መጨረሻ አሸናፊ የሚሆኑት ሀቀኞች ናቸዉ፡ የተረሱ ቆራጥ ሰማእታትንም ታሪክ ያስታዉሳቸዋል።

ባለፈዉ ለዋና ድርጅታዊ ጉባኤ ሁላችንም ወደኤርትራ ያደረግነዉ ጉዞ ከድሮዉ ለየት ያለ ነበር፣ ከዉጭ የመጣነዉ ሶስት አይነት አላማ የያዘ ቡድን ነበር፣

አንደኛዉ እነ አቶ ዘዉዳለምና ኮ/ል ጌትነት፡ አቶ ጥላሁን፡ አቶ መልኬና ሌሎችም ያሉበት ነዉ።

አመጣጣቸዉም የየግላቸዉን ወይም የግሩፓቸዉን ጥቅም ታርጌት አድርገዉ ነዉ፡ ከሁለት አንዱን እንዳያጡ ተጠንቅቀዉ ነበር።

ፕ/ር መሀሪን ለጉባኤዉ አስመራ እንሂድ ሲሉት አይ ላርበኞች ጉባኤ አልሄድም, ከሄድሁ ያርበኞች መሪ ከምትሏቸዉ ጋር አልነጋገርም, የምነጋገረዉ ከኤርትራ ባለስልጣናት ጋር ነዉ, የምነጋገረዉም የቀሩትን አርበኞች ለኛ እንዲያስረክቡንና, በነፃነት ምርጫ አካሂደን ያለምንም ተፅኖና ጣልቃ ገብነት እኛ ከመራነዉ ባጭር ግዜ ድርጅቱን የት እንደምናደርሰዉ ታያላችሁ ይላቸዋል፣ ጣዲያ ይህ ቢሆንምኮ ሹመት ማግኘታችን አይቀርም ብለዉ በፕሮግራሙ ይመሰጣሉ።

ፕሮፌሰሩም, እኔ ሳልሄድ ይህን ሀሳብ ለኤርትራ ባለስልጣናት አድርሳችሁ ተስማምታችሁ መምጣት የምትችሉ ከሆነ ሂዱና ሞክሩ, ባይቻል እንኳ እኛ የመሰረትነዉን ድርጅት እዉቅና እንዲሰጡንና እኛም እንድንታገል የሚል ግልፅ የተቀደሰ ሀሳብ ሲያወያያቸዉ ከመቅሰፍት ግልብጥ ብለዉ እሽ እናደርሳለን እናስፈፅማለን ካንተም ጋር እንሰራለን አሉ።

ባዲስ ድርጅት አዲስ ስልጣን ሊያገኙ ፈልገዉ ሳይሆን ይቀራል?

ሁለተኛዉ፣ የነልኡል ቡድን ነበር አመጣጡም, በቸልታ ምንም አዲስ ነገር እንደማይኖር, ተረድተዉ ግን እስኪ እንሂድ ባይሆን እንኳ የራሳችን ፓርቲ መስርተን ቦታ እንጠይቃለን እንጅ ካርበኛዉ ጋር መስራት እንደማይቻል ቀደም ብለዉ የደመደሙ ናቸዉ፡ ግንባር እያሉ ሰራዊቱ ያለበትን የተወሳሰበ ያመራርና የነፃነት ችግር ቢያስደነግጣቸዉም, ዉጭ ካለዉ አባላት ጋር ጠንክረን እናስተካክለዋለን ብለዉ አስበዉ ነበር፡ አዉሮፓ እንደደረሱ መንቀሳቀስ እንደጀመሩ, ያ ሁሉ ሽማግሌና ምሁራን የተልፈሰፈሰ ሁኖ ሲያገኙት ነገሩ ሁሉ ግራ ይገባቸዋል። በዚህ የተነሳ ነዉ ለብቻ እንስራ? ወይስ ምን ይሻላል የሚል ዉዥንብር ዉስጥ የገቡት፡

ሶስተኛዉ የነስለሽና የነኤልያስ ቡድን ነዉ አመጣጡም በሙሉ ልቦናቸዉ ላርበኛዉ ጉባኤ ሆኖ, ግን የአርበኛዉ ያሰራርና ያመራር ችግር ይሻሻል ይሆናል ብለዉ የሚያስቡ ናቸዉ።

ይህ ቡድን ያርበኞች ግንባር ከዉጭ እስከ አስመራ እላይ ያሉት በሙሉ በጎንደሬዎች የተሞላ ሆነ ብለዉ የሚያጉረመርም ነበር፣ እዉነታቸዉን ነበር፣ ይህ የጎንደሬነት መሰባሰብ ገደብ ተሰጥቶት የኢትዮጵያዊነት ስብስብ እንዲሆንና፡ ያርበኛዉ አመራርም ችሎታ ባላቸዉ እንዲተካ የሚል አስተሳሰብ ያላቸዉ ነበሩ፡ ችግራቸዉ ግን በተለይ ስለአርበኛዉ አመራር በተናጠል ማዉራት ብቻ እንጅ፡ በከረረ መልኩ በስብሰባ አይናገሩም።

የነ አቶ አለምዘዉድ, ኮ/ል ጌትነት, አቶ ጥላሁን, አቶ መልኬ ያሉበትን ቡድን ምንነቱን ለማወቅ ግራ የሚገባ ነዉ፣ እንደ ሀገርና አላማ ሳይሆን የሚያስቡት እንደ ግል ጥቅም ወይም ስልጣን ነዉ፡

መጀመሪያ አርበኛዉ ተወዳዳሪ የለለዉ ድርጅት አድርገዉ ይፎክሩና ደፋቀና ይሉ ነበር።

ፕ/ር መሃሪ ስለአዲስ ድርጅት ሲያማክራቸዉ ግልብጥ ብለዉ ያን ሀሳብ ለማስፈፀም አስመራ ሄዱ፡

አስመራ እንደሄዱ ሻብያ ደካማ ጎናቸዉን አዉቆባቸዉ፡ ማእከላዊ ኮሚቴ አድርጎ ሲሾማቸዉ ከፕሮፌሰሩ ጋር የመከሩበትንና የተስማሙበትን ፕሮግራም እርግፍ አደረጉት። ካረጁ አይበጁ, የተባለዉ ለዚህ ነዉ፡

የነልኡል ቡድን ካርበኛዉ ጋር መስራት የማይቻልበትን ዋና ችግሩን አብራርተዉ መናገር አይደፍሩም፣ ለሚቀርቡት ሰዉ ብቻ ትክክለኛ አስመራ ያለዉን ችግር ይናገራሉ በስብሰባና በአመራሩ ላይ ግን ትንፍሽ አይሉም ለምን ይሆን?

የነስለሽና ኤልያስ ቡድንም እንደዚሁ መዋቅር ይስተካከል ከማለት ዉጭ ደፍሮ መሰረታዊ ችግሮችን አይናገሩም በተናጠል ግን አርበኛዉ እንዴት ፖለቲካ ችሎታ በሌላቸዉ ሰወች ይመራል መአዛዉ ሊቀመንበር መሆን ያስወቅሰናል ይላሉ።

የድርጅቱ ትክክለኛ ችግር ነዉ፡ ግን መልስ ከሚሰጠዉ ቡድን ጋር በግልፅነት የመነጋገር ሞራልም ድፍረትም የላቸደዉም።

ታዲያ ሁሉም ቡድኖች፡ የሞራልና ያላማ ጉድለት ነዉ ያላቸዉ፡ እነ ሻ/ል ዘዉዱ ኮ/ል ታደሰ እና ዮሴፍ አማራጭ ሳይኖራቸዉ እዛዉ እያሉ ለሀገር ለወገን ብለዉ ያን ያክል ሞራልና ድፍረት ሲኖራቸዉ፣ እኛ ግን ያሜሪካና ያዉሮፓ ዜግነት ይዘን ሻብያ ምንም እንደማያደርገን እያወቅን እንልፈሰፈሳለን፣ ያሳዝናል።
እንደዚህ አይነት የተበታተነ አላማና ሀሳብ ይዞ ነበር ያሁሉ ሰዉ ካሜሪካና አዉሮፓ አስመራ ለጉባኤ የገባዉ።
ታዲያ ያን ሶስት አይነት አላማ ይዞ የመጣዉን ቡድን, ሻብያ ሸወዳቸዉ ሁሉም እርስ በርስ እንዲጨራረሱበት ቦንብ ቀብሮ ላካቸዉ፡
የጉባኤዉ ግዜ ሁሉንም ከዉጭ የመጡትን ባጠቃላይ የአርበኞች ግንባር የማእከላዊ ኮሚቴ አድርጎ ሾማቸዉ፣ ከዛ በፊት ከዉጭ አባላት ማንም ማእከላዊ ኮሚቴ አልነበረም፡ ለጉባኤ አስመራ ያልመጡትንም እንቅፋት ይሆኑብኛል ድርጅቱን ይበትኑብኛል ብሎ የፈራቸዉንም እነ ፕ/ር መሀሪን በስልጣን የሚደለሉ መስሏቸዉ ሾሟቸዋል።
ይባስ ብሎ ለመደለያ ፕ/ር መሀሪን ያርበኞች የዉጭ ጉዳይ አደረገዉ፡ ታዲያ ሁሉም የማእከላዊ ኮሚቴ ተብሎ ሲመረጥ ስለተደሰቱ ሌላዉን አጀንዳቸዉን እርግፍ አድርገዉ ተዉት፡
ጉባኤዉ ሲጠናቀቅ ብዙ ተወራለት ተፎከረበት እልል ተባለለት፡
ቆይቶ ግን ሁሉም ወደየ መጣበት እንደተመለስ ትንሽ ሰነባብቶ, ሻብያ የቀበረዉ ቦንብ ፈንድቶ, እርስ በርስ መዘላለፍ መቆራቆስ መበታተን ተፈጠረ፡

**ጨዋታ ፈረሰ, አባይ ደፈረሰ፣ የሚባለዉ የልጅነታችን ጨዋታ ትዝአለኝ፡**

የጥሉን አጀማመር አቶ ልኡልና አቶ ደምስ ፓል ቶክ ላይ ቀርበዉ አዳብራሩት, ብዙዎቻችሁ ስምታችሁታል።
እነ አለምዘዉድና ኮ/ል ጌትነትም ሹመት ሲሰጣቸዉ ግዜ ፕሮፌሰሩ የሰጣቸዉን መልእክት እርግፍ አድርገዉ ተዉት፡ ለማካካሻ ለመደለያ የሚሆን, ፕሮፌሰሩን እየዉ የዉጭ ጉዳይ አስደርገን አሾምንህ አሉት፡
እግዚያብሄር ይስጠዉና ፕሮፌሰሩ, ሹመት መች ፈለኩ በሻብያ የሚመራ ድርጅት ማገልገል አልፈልግም ቅንነት ቢኖራችሁ, እኛ ያልናችሁን አገራዊ አደራ የያዘ መልክት ማድረስ ነበረባችሁ፣ በሉ ሹመቱን ወዲጣ ጣሉት፡ በሀገርና በህዝብ ላይ ቁማር አልጫወትም ይላቸዋል።
ለካስ መጀመሪያም, እኛ ብዙ አስመራ ተመላልሰን ሳንሾም እሱ ተሾመ፣ ያዉም በለለበት ብለዉ በልባቸዉ አኩርፈዉ የነበሩት ሽማግሌዎች, ይህን ሲላቸዉ እነሱ ለመሾም የዉጭ ኮሚቴዉን ሳያማክሩ በድብቅ አስመራ ሄደዉ ፕሮፌሰሩ አልፈልግም ብሏል እኛን ሹሙን ይላሉ፡ እጅ መንሻም አስር ሺህ ዶላር ይከፍላሉ፣ ሻብያም መንገድ ሲከፈትለት እሽ ብሎ የዉጭ ኮሚቴ ሊቀመንበር፡ ፀሀፊ፡ ገንዘብ ያዥ አድርጎ ሾሞ ይልካቸዋል።
ታዲያ ሻብያ ይህን ሲያደርግ እረብሻ እንደሚነሳ በትክክል ያዉቃል፡ ግን, እረብሻዉን ስለፈለገዉ ነዉጅ፡
ምክንያቱም በመጀመሪያዉ መለስተኛ ጉባኤ እርስ በርስ ይፋጁ የነበሩት የነልኡልና የነ ስለሽ ቡድን, እንዲሁም ሽማግሌዎች, ሁሉም ኮሚቴ ማለት ይቻላል፣ በዋናዉ ጉባኤ ግዜ ሰላም ወርዶ ቀዝቀዝ ብለዉ አስመራ ላይ ያለድሯቸዉ አብረዉ ሻይ ቡና ሲባባሉና, ሲጫወቱ ሻብያዎች ስለታዘቡ አንድነት ተፈጠረ ብለዉ ደስ አላላቸዉም ነበር።
ወዲያዉ ተመልሰዉ ይመጡና የዉጭ ኮሚቴዉን, እኛ ተሹመናል ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ, የዉጭ ኮሚቴዉን የምንመራዉ እኛ ነን ይላሉ፡ ዱብ እዳ የሆነባቸዉ, አስመራ በጉባኤ ተመርጦ ተዋቅሮ የመጣዉ የዉጭ ኮሚቴ ሁሉ ግራ ይገባዉና፣ ሳታማክሩንና ሳታሳዉቁን ለምን ሄዳችሁ፣ ፕ/ር መሀሪ እምቢ ቢል እኛ ከዚሁ ተሰብስበን መምረጥና ለአስመራ ቢሮ ማሳወቅ እንችል ነበርኮ, ይላሉ።
ተሾምን ባዮች ደግሞ, አይ በቃ ሆኗል አልፏል , ልቅስ 10.000 ዶላር ሰብስበን አሚልተን ለድርጅቱ ሰጥተን መጥተናል፣ አሁን ተሎ ብላችሁ እያንዳንዳችሁ 200ዶላር ባስቸኳይ ክፈሉ፡ በየበኩላችሁም ከምትቀርቧቸዉ አሰባስቡ ተብላችኋል ይላሉ፡ ሁሉም አንከፍልም, ህጋዊ የሆነ የገንዘብ አሰባሰብ አሰራር ሳይወጣና ህጋዊ ባንክ ሂሳብ ሳይከፈት እንደድሮዉ ብሉት ብለን አንከፍልም ይላሉ፣
እዚህ ላይ የነ ኮ/ል ጌትነትና አቶ ያለምዘዉድ ቡድን ሳይሸወድ አልቀረም፡
ዶላሩን ለመክፈልና ለመሾም, ካስመራ ሰወች ጋር የሽዎዳ ስምምነት ሳያደርጉ አልቀሩም፡ ዶላሩን እኛ እንክፈልና, ግን ለዉጭ ኮሚቴዉ ሁሉም ባስቸኳይ በየፊናዉ ገንዘብ አሰባስቦ ለኛ እንዲሰጠን ትዛዝ አስተላልፉልን፡ ያን የምንቀበለዉን ገንዘብ ለከፈልነዉ ለራሳችን እንተካዋለን በሚል ተስፋ ነዉ ዶላሩን መዥልጠዉ የከፈሉት። **የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች ማለት እንዲህ ነዉ።**
ከዚህ በኋላ ነዉ እንግዲህ ነገሩ እየጠከረረ እየሰፋ መጥቶ በየሚዲያዉና በየከተማዉ እርስ በርስ መወዛገብና አንዱ አንዱን አባረናል መባባል የጀመሩት፣

ዉድ አንባቢያን እስካሁን እንዳነበባችሁት የችግሩ መሰርታዊ ምንጩና አባባሹ ማንና ምን እንደሆነ ሳትረዱ አልቀራችሁም።
እነዚህ አዲስ የማእከላዊ ኮሚቴ ነን የሚሉ የዉጭ ኮሚቴዎች ሁሉ እርስ በርስ እንዲነታረኩ ያደረጋቸዉ ምንጩና ችግሩ ምን እንደሆነ በልባቸዉ ችግሩን ያዉቁታል።
አርበኞች ግንባር በራሱና በኢትዮጵያዊ አጀንዳ ችሎታ ያለዉ መሪ ስለሌለዉና፣ እንደድርጅት በፅሁፍ የተቀመጠ ህገደንብ አለዉ ቢባልም, ማንም ግን የሚያዉቀዉና የሚመራበት የለም፣ ልክ እንደወያኔ ህገመንግስት አረቀኩ ብሎ ስራ ላይ ዉሎ እንደማያዉቀዉ, እነ መለስ ለራሳቸዉ ስልጣን የሚመች መመሪያ ለየመስሪያቤቶች እንደሚያስተላልፉ ሁሉ፣ ላርበኞች ግንባርም፣ ሻብያ ለራሱ የሚመች ያሰራር ደንብ ነዉ እንጂ ለአባላቱ የሚያሰራጨዉ, የድርጅቱን መመሪያ ደንብ አያሰራጭም፣

እንግዲህ፣ አጥፊዉንና የጥፋቱን መነሻ ምንጭ እያወቁ ሁሉም, እከሌ ነዉ እሱነዉ እየተባባሉ መወቃቀስ ምን ይሉታል? የሞራልና የራስ መተማመን መንፈስ ካላቸዉ ለምን አስመራ ያለዉን ችግርና ተፅኖ አይናገሩም፣ ለዛ ጥፋት ዋና አስተዋፅዎ ያደረጉትን ያስመራን ሰወች ከዉዝግቡ ዉስጥ ስማቸዉን ለምን አይጠቅሱም፡

ወገኖቸ እንግዲህ ጥፋቱንና አጥፊወችን ካወቅን እነዚህን አጥፊወች ስማቸዉንም የጥፋት ድርሻቸዉንም እየጠቀስን እንዉቀሳቸዉና ከጥፋታቸዉ ታርመዉ ህዝብን ይቅርታ ብለዉ የሚቻል ከሆነ ድርጅቱንም እንደገና እንድናነቃቃዉና በነፃነት እንድንመራዉና ለድል እንድናበቃዉ።
በአስመራ ያሉትን ወንድሞቻችንም እንዲለቀቁልን፣ ካለበለዚያ ሻብያ አስመራ ላይ እየወጠነ ያለዉ በብሄር መከፋፈል ስራ እጅግ አደገኛ እየሆነ ነዉ።

በተለይ አቶ ዘዉዳለም፣ አቶ መልኬ መንግስቴና እንዲሁም ሌሎች ጓደኞቻቸዉ፣ በአቶ መስከረምና፣ ፕሮፌሰር ሙሴ ተገኝ አማካኝነት, ሻብያ የግንባሩን አመራር እየበታተነ, ምርጥ ወንድሞቻችን እየታፈኑ ሲገደሉ, ሲባረሩ, አንድም ቀን ለወገን ለህዝብ ሳታሳዉቁ ዝም ብላችሁ ከሻብያ ጋር እየተለሳለሳችሁ መቆታቸሁ ታላቅ በደል በሀገርና በወገን ላይ ፈፅማችኋል፣ አሁንም እየፈፀማችሁ ነዉ፡ ይህ በደል በነበረበት ግዜ እነአቶ ስለሽም ደርሰዋል።
እነ አቶ ተስፋዬና, አቶ ሽባባዉ አበበ, እንዲሁም ብዙ የቁርጥ ቀን ወንድሞቻችን ሻብያ ለምን ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ያዛችሁ ብሎ አፍኖ ሲገድላቸዉ እያወቃችሁ ዝም ማለታችሁ ታሪካዊ ጥፋት ነዉ፡

አቶ ይሄነዉ ሁነኛዉና ምርጥ ጓደኞቹ, የሻብያ ጣልቃ ገብነት ይቁም ብለዉ ስለተከራከሩ, ኮ/ል ፍፁምና መስከረም አታላይ ሊረሽኗቸዉ ሲሉ አምልጠዉ አገራቸዉ ገብተዉ አንዳንዶች ለወያኔ ይቅርታ ብለዉ ሲገቡ እነ ይሄነዉ ግን, ወያኔን ይቅርታ አንልም ብለዉ, ቋራ በረሀ ሸፍተዉ ብቻቸዉን ሲዋጉ ከርመዉ, ምርጫ 97 ግርግር ሲፈጠር ባህርዳር ገብተዉ እርምጃ ሊጀምሩ ሲሉ, ወያኔ ይሄነዉንና 5 ጀግና ጓደኞቹን እረሽኖ ሜዳላይ የጣላቸዉ እናንተ በሰራችሁት ግፍና በደል አደለም? ነፃነት ቢኖርና ባይበደሉ ይሄዱ ነበር?
እነ ልኡል ቀስቅስ የወያኔን የፓርላማ ጥሩ ደመወዝ ይቅርብን ብለዉ, ሊታገሉ አርበኛዉን ሲቀላቀሉ, የሚያሰራቸዉ ተስፋ ቢኖር ወደ ዉጭ አይሄዱም ነበር፡ አቶ ልኡል, በድሮዉ ጦር ከመድፈኛ ተዋጊ እስከ እዉቅ መድፈኛ አዛዠ እንደነበረ እያወቃችሁ, እነዚህን ልምድ ያላቸዉ ባለሙያወች ማሰራት አልቻላችሁም፡ ሻብያም ወደ ዉጭ እንዲሄዱ የፈቀደላቸዉ ለተንኮል ነዉ፡ ችሎታ ያለዉ ሰዉ ካጠገቡ ስለማይፈልግ ነዉ።

አቶ ዘዉዳለም ከ80 አመት በላ ሆነዉ የሶስት መንግስት እድሜ እያለወት እንደ አባት ብቻ ሳይሆን እንደ አያትም ነዎት። ታዲያ ኢትዮጵያዊ የሆነዉን ድርጅት ሻብያ እየመራዉ ወንድሞቻችን ተገድለዉ, ተስፋ የነበረዉ ድርጅት ሲዳከም እያወቁ ዝም ብለዉ ሻብያን እያዳመቁ መቆየትዎ ለምን ይሆን? ወንድ ልጅዎ ኤርትራዊት ያስመራ ልጅ ስላገባና ስለተዋለዱ ይሆን? ያዉም ከሻብያ ዋና ጄኔራሎች አንዱ የልጅዎ ሚስት አጎት ስለሆነ ይሆን? እኛንና አገርዎን ባይፈሩ እንኳ የቀረወትን እድሜ ፈርተዉ ይናዘዛሉ ንስሀም ይገባሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። እባካችሁ አሬና በረሀ እየማቀቁና እያለቁ ያሉት ዉድ ወንድሞቻችን እንደናንተ ትርፍ እድሜ አደለም እየኖሩ ያሉት፡ ወጣትነታቸዉን እንኳ ሳያጣጥሙ, ለሀገር ብለዉ ነዉ እዛ የሄዱት፡

አቶ ኤልያስ ክፍሌ፣ ባንድ በኩል በምታደርገዉ የሚድያ ስራ በጎ ነገር እየታየብህ፡ ብዙ ግዜ ግን ያልተደረገ ያልተባለ ዜና ካስመራ ሲላክልህ, ሻብያን ለማስደሰት ብለህ እየጨማመርህ አጋነህ እየፃፍክ ህዝባችን ዉዥንብር ዉስጥ ከተህ ትልቅ ጥፋት ሰርተሀል፡
ሚዲያ ምን ያህል ሀይል እንዳለዉ ታዉቃለህ፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያዉያን በከባድ ጭቆና ያለን ህዝቦች ስለወያኔ የተወራዉ ሁሉ እዉነት እየመሰለን, ወደ ተወራበት እንሄዳለን፡ በዚህ የሀሰት ዘገባ ስንቶች ኤርትራ ገብተዉ አልዋል፡ አሁንም እያለቁ ነዉ፡
ያለህን አቅምና እዉቀት ተጠቅመክ፣ አስመራ ያለዉን ያርበኞች አመራር በጣም የደከመ መሆኑን ተገንዝበህ, መፃፍ ነበረብህ፡ ስላርበኞች ግንባርም አጠቃላይ ስራ ሂደት ከሻብያ አመራሮች ጋር እየተነጋገራችሁና መመሪያ መቀበላችሁ ስህተት መሆኑን እያወቅህ, ዝም ብለህ አዳማቂ ሁነህ መቆትህ, ስህተት ብቻ ሳይሆን እያወቅህ የሆነ ተልኮ ያለህ ያስመስልብሀል፣ ህዝቡም ይጠረጥርሀል፣
ምክንያቱም ያለህ የትምህርት ደረጃና አስተዳደግ, ይህን ያሰራርና ያለዉን የከፋ በደል ለመረዳት ብቻ ሳይሆን፣ ድርጅቱንም ልትመራዉ የሚያስችል እዉቀትና አቅም አለህ።
ሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶችን ትንሽ ሲሳሳቱ መአት እየወረድህባቸዉ፡ ያርበኞች ግንባር ዉስጥ ግን ያን ያክል በደልና ስህተት ሲሰራ ለምን ዝም ማለት መረጥክ?
ሁል ግዜ ስለ ኢሳያስ የአመቱ ምርጥነት ከመፃፍ, ምናለ, የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅት አመራሮች በየአመቱ እያወዳደርህ ምርጥ የአመቱ የድርጅት መሪ ብለህ ብታወጣ?፣
ምናልባት ባለቤትህ የልጅህ እናት ኤርትራዊት ስለሆነች ይሆን?፣ ያዉም አባቷ የኢሳያስ አፈወርቂ አንድ መንደር አብሮ አደግ ስለሆኑ ይሆን? እባክህ, ለሀገር ለወገን ብለዉ አሬና በረሀ ላይ በሻብያና በወያኔ አጣብቂኝ ዉስጥ ገብተዉ እየሞቱና እየተሰቃዩ ያሉት ንፁህ ወንድሞቻችን ናቸዉ፡ እንደኛ የጠገቡ የደላቸዉ አደሉም፣

አቶ ስለሽ ጥላሁንን፣ ተጠያቂ የሚያደርገዉ ግንባር ድረስ ተመላልሷል፣ ከነ ፕሮፌሰር ሙሴና መስከረም አታላይ ጋርም አብሮ ሰርቷል፣ ታዲያ እነዚህ ሰወች በሰራዊቱ ላይ የሰሩትን ጥፋት እያወቀ ለምን አፍኖ ዝም

አለ፣ ድርጅቱ በሻብያ እየተመራ እያየ ይህን ያክል አመት አብሮ አስረሽ ምችዉ ማለት ምን አይነት ትግል ነዉ? እነ መስከረም ያን ያክል በሰራዊቱላይ የጭካኔ በደል የሰሩት ከነ ኮ/ል ፍፁም ጋር ስለሆነ, ስለመስከረም ካነሳሁ ኮ/ል ፍፁምም መነሳቱ አይቀርም ስለዚህ ዝም ብል ይሻላል ብለህ ነዉ?
ሻብያ እርትራ ዉስጥ ያሉትን ተቃዋሚዎች በዘር ከፋፍሎ እንደሚያኖራቸዉ እያወቅህ፡ የተንኮል መሆኑ አልገባህ ብሎ ነዉ?
ኢሳያስን ቃለ መጠይቅ ስታደርጉት የሰጠዉ መልስና ኤርትራ በተግባር እየተደረገ ያለዉ ተገላቢጦሽ መሆኑን በደንብ እያወቅህ እስካሁን ዝም ማለትህ ጥፋት መሆኑን አልተረዳህም?
ከቃለ መጠይቁስ በኋላስ, በተግባር የተሻሻለ ነግር አለ ወይስ የለም የሚል ነገር ለምን አላሳወክም።
ባለፈዉ ግዜ ሎንዶን ላይ ኢትዮጵያዉያንና ኤርትራዉያንን ለማቀራረብ በሚል ፕሮግራም አዳራሽ ተከራይተህ ስብሰባ ጠርተክ ደፋቀና ስትል ነበር፡ ሀሳቡ መልካም የተቀደሰ ቢሆንም፡ ቅድሚያ የሚሰጥዉ አልነበረም፣ አንገብጋቢና ወቅታዊ ለሆኑት ለሚከተሉት ለምን ቅድሚያ አልሰጠህም?
1ኛ-ከዛ የባሰና አንገብጋቢ የሆነ የራስህ አገር ሰወች ከግዜ ግዜ በዘር በጎሳ በቡድን  ጎራ እየለዩ እየተራራቁ፣
2ኛ-የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች ከግዜ ግዜ ልዩነታቸዉ እየሰፋ አብሮ መስራት እየተሳናቸዉ።
3ኛ-እራስህ የተሰለፍህበት ድርጅት አርበኞች ግንባር ያን ያክል የቦነነ ኪሳራ ዉስጥ ገብቶ አመራር ነን የሚሉት ልዩነታቸዉ ከግዜ ግዜ እየሰፋ እየሄደ፣

4ኛ-ሻብያ እራሱ የሁለቱን አገር ህዝቦች ልዩነት ሆን ብሎ እያሰፋዉ በሚገኝበት ወቅት, አቶ ስለሽ የሁለቱን ህዝቦች ለማቀራረብ ብሎ የገንዘብና የግዜ ኪሳራ ዉስት መግባትህ ትልቅ ስህተት ነዉ።
ይልቁንስ በዚህ ያዳራሽ ወጭና ግዜ, ያገርህን ሰወች ከተለያዩ ብሄሮችና የፖለቲካ ድርጅቶች ያገር ሽማግሌወች ስብሰባ ብትጠራና፣ የመቀራረብና አብሮ የመስራት ችግሮች ምንድናቸዉ እባካችሁ, ኑና እንወያይ ብትል ወቅታዊና አስፈላጊ ስለሆነ ትከበራለህ ትሞገሳለህ፡ ብዙ ሰዉም ይመጣልህ ነበር፡ ባይመጡልህም እንኳ, ለታሪክ ወሳኝ በሆነ ወቅት ድርሻህን መወጣትህ ይመዘገብልህ ነበር።
አቶ ስለሽ ጥላሁን፡ ከሁሉም ትንሽ ደፊር የማለት ነገር ይታይብሀል፡ የሻብያን እስትራቴጂ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ፣ ከሻብያዎች ጋር ለብቻ ሻይ ቡና በምትሉበት ሰአት, ያርበኞች ግንባር መሪወች ብቁ አደሉም፣ በነ መአዛዉና በሌሎቹ አቅም በሌላቸዉ ሰወች እየተመራ ድርጅቱ የት ሊደረስ ነዉ፣  አቅም ያለዉ ሰዉ እኮ ሞልቷል ሌላ ይሾም፡ ምክንያቱም ብዙ ሰዉ እንዴት በነ መአዛዉ ማንበብና መፃአፍ በማይችሉ ሰወች ድርጅቱ ይመራል እያሉ እያጉረመረሙ ነዉ ብለክ በተደጋጋሚ እንደተኛገርሀቸዉ ሰምተናል፡ ታዲያ ይችን አባባል ጠቅላላ ስብሰባ ላይ አልተናገርሀትም?
እንዲያዉም ምን ሰማን, ስለሽ እነ ወዲ ምስግናን፣ ለምን እነኮ/ል ታደሰ ወደ ድርጅቱ ተመልሰዉ ድርጅቱን አይመሩትም ብሎ ድርቅ ብሎባቸዉ ነበር፣ ነገሩ እዉነት ሆኖ ከኛ አልፎ በረሀ ያሉት የቀሩት ሰራዊት ሰምተዉት ኮ/ል ታደሰ ሊመለስ ነዉ ብለዉ እልልታ በእልልታ ሆነዉ እንደነበር የታወቀ ነዉ።
ታዲያ ቆየት ብሎ ምን ሰማን, ወያኔ የመሬት ፖሊሲህን ቀይር ሲባል፡ በኢህዴግ መቃብር ላይ ነዉ የሚቀየረዉ እንደሚለዉ፣ ያስመራ የሻብያ ሰወችም እነኮ/ል ታደሰ አርበኛዉን የሚመሩት በሻብያ መቃብር ላይ ነዉ አሉና አሳረፉን።

አቶ ስለሽ የዉጭ የድርጅት ጉዳይ ሀላፊና በእንግሊዝ የአርበኞች ቻፕተር ሀላፊም ሆኖ እያለ, ያስመራ ተንኮለኞች ሆን ብለዉ ሎንዶን ለሚኖር ሌላ አባል ለአቶ ዮሴፍ ለሚባል, የሎንዶን ያርበኞች ተወካይ ብለዉ በጎን ደብዳቤ ሲልኩለትና, ሎንዶን ላይ ተደጋጋሚ ስብሰባ ሲጠራ፣ ስለሺ ደብዳቤ የፃፉትን አስመራ ያሉትን እነ ወዲ ምስግናንና ኮ/ል ፍፁምን መክሰስና መዉቀስ ሲገባዉ, ከፍርሀት ይሁን ከምን, እነሱን ትቶ ከሎንዶኑ ከአቶ ዮሴፍ ጋር ዱላ ቀረሽ ጥል ዉስጥ ገቡ፣
አቶ ዮሴፍ፣ በጎን ተደዋዉሎ ደብዳቤ ማፃፉን ከየት ተማረዉ? ሌሎች ትላልቆቹ በጎን እየተደዋወሉ የሚሰሩትን እያየ፣ የማይወራረድና የት እንደሚገባ የማይታወቅ ገንዘብ ሁሉም ዉጭ ያለ ያርበኞች አመራር ነኝ የሚል ሲሰበስቡ እያየ እሱም እኔስ ከማን አንሳለሁ ብሎ ስብሰባ መጥራቱና, ገንዘብ መሰብሰቡ ከሌሎች አመራሮች ጥፋት ምኑ ይለያል?
አቶ ስለሽ፣ ይህን ነገር ያስመራ ሰወች ሆን ብለዉ እንደሚያደርጉት ከጓደኞችህ ጋር በግልፅ እየተነጋገርህ, የትግሉ ባለቤት ለሆነዉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግን በሚዲያም ይሁን በተመቸህ መንገድ ለማሰማት ባለመሞከርህ, እስካሁን ሻብያ ብዙ ንፁህ ወንድሞቻችን ከማጥፋትም አልፎ፣ ልክ እንደወያኔ፣ ዲያስፖራዉ እርስ በርስ እየተናከሰ ልዩነቱ እንዲሰፋ እያደረገ መሆኑን እያወቅህ ዝም ማለትህ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ሰርተሀል።
**ስለሽ፡ ችግርህ ምን ይሆን? ፍርሀት? ጥቅም? ስልጣን? አንተን ከነዚህ ሁሉ ለመመደብ ይከብደኛል ስትፈራም አላየሁህ ገንዘብ ስትቦድስም አላየሁህም አልሰማሁምም እንደሌሎች በጋብቻም የተነካካህ መሆንህንም አላገኘንብህም ታዲያ ምንድነዉ ሻብያን ማዳመቅህ? መልስህን ባደባባይ እንጠብቃለን።**

ሌላዉ የነ ልኡልና አቶ አሰፋ ቡድን ነዉ፣ እነዚህ ሰወች ከሁሉም የበለጠ ከሰራዊቱ ጋር በረሀላይ ከአንድ አመት ያላነሰ ተቀምጠዋል፣ እነሱ በነበሩበት ግዜ ትንሽ በዛ ያለ ሰራዊት ነበር እንዳሁኑ ሂዶ አላለቀም ነበር፣ ስለዚህ እነ አቶ ልኡል ሰራዊቱ ያለበትን ጭቆናና ያስተዳደር በደል እንኳን እነሱ በነበሩበት ወቅት ቀርቶ, እነሱ ከነበሩበት በፊትም የነበረዉን የሰራዊቱ መከራና ችግርም በደንብ ያዉቃሉ፡
የሻብያ ባለስልጣኖች ሰራዊቱን እንደፈለጉ እንደሚያደርጉት በደንብ ታዉቃላችሁ ስለሞቱት ስለታፈኑት ሰወች በደንብ ታዉቃላችሁ፡

ታዲያ ወደ አዉሮፓ እንደገባችሁ ያርበኞች የዉጭ ጉዳይ ተወካይ ነን እባካችሁ እርዱን አባልነት ተመዝገቡ እያላችሁ ካሜሬካ እስካዉሮፓ መቀስቀሱ ምንድነዉ?
ግንባሩ ያን ያክል እየደከመ እየተበታተነ ባለበት ወቅት, ቅድሚያ ችግሩን አጋልጦ ድርጅቱን ከመፈራረስና ከመበታተን ለማዳን መንቀሳቀስ ሲገባችሁ፣ የአባላት ምዝገባና የገንዘብ መዋጮ ለማካሄድ ደፋቀና ማለት ትልቅ ታሪካዊ ጥፋት አጥፍታችኋል፡
ከናንተ ጋር ወደ አዉሮፓ የሄዱት ጓደኞቻችሁማ አርበኞች ግንባር በሻብያ ማነቆ ስር መሆኑን ስለተረዱ ምንም ማድረግ ስለማይቻል ዝም ብለዉ የግል ኑሯቸዉን መኖር ጀምረዋል፡ እነሱም ቢሆኑ ዝም በማለታቸዉ በታሪክ ተጠያቂ ናቸዉ፡ እንደናንተ ባይሆኑም።

ይህን የዉጭ ጉዳይ ስራ ተወክለን መጣን ብለዉ ደፋቃና በሚሉበት ወቅት ነበር ከነስለሽ ግሩፕ ጋር አይንህን ላፈር ያሰኘ ጥል ዉስጥ የገቡት፣ እነስለሽ እኛ ቀደምቶች እያለን ለምን ለነሱ ስልጣን ተሰጠ በሚል ነዉ የተነሳሱት ይባላል፣
እነ ልኡል ከነ አለምዘዉድ ጋር ሆነዉ፣ እነ ስለሺ ኢልያስና ደምስ ባንድ ወገን ሆነዉ የዉጭዉን አባላትን ከሁለት ከፍለዉ እኛ ነን እኛ ነን በሚል የተፋጁት፣

በ2009 ለመለስተኛ ጉባኤ አስመራ በሄድንበት ወቅት, ያንዱ ግሩፕ ተሹሞ መፍትሄ ያገኛል, ሁለቱ ግሩፕ ይታረቅና, ሰላም ይሆናል ተብሎ ተስፋ ሲደረግ፣ ሻብያ ግን፣ የባሰዉን ተደርጎ በማይታወቅ አሰራር ችግሩን ከሁለት ግሩፕ ወደባሰ ብዙ ግሩፕ የሚበትን መመሪያ ሰጥቶ ሸኘን።

መመሪያዉም እንዲህ ነዉ፣ የሁሉንም ቡድን የዉዝግብ መንስኤ ካደመጡ  በኋላ, የዉጭ ተጠሪ የሚባል ነገር የለም ሁሉም አባላት በያለበት አገር በግሉም በቡድንም እሆነ ድርጅቱን ለማጠናከርና ለማስፋት መስራት አለበት፣ የዉጭ ተጠሪ የሚባል አያስፈልጋችሁም፣ ሁሉም ተጠሪነቱ ለአስመራ ነዉ, ሁላችሁም የሰራችሁትን ወደኛ ሪፖርት አድርጉ ተብለን አረፍነዉ።
ሁሉም ትንፍሽ ሳይል እሽ ብሎ ወደመጣበት ተመለሰ፣ ከዛ በኋላ ነዉ ከሁለት ግሩፕ ወደ ብዙ ግሩፕ አልፎም በየግል በምድረ አዉሮፓና አሜሪካ ያርበኞች ስብሰባ አለኝ ተገኙልኝ መባል የተጀመረዉ፣
የለንደኑ አቶ ዮሴፍም ከዚያች ቀን ጀምሮ በሰፊዉ ለብቻዉ ያርበኞች ተወካይ ነኝ እያለ ሲቀሰቅስ ስለሽም ባንድ ጎን ይቀሰቅሳል ያዉሮፓዎችም የአሜሪካዎችም እንዲሁ።

በዛን ወቅት ነዉ እነ ልኡል በረሀ እያሉ ያዩትና, ዉጭ ሄደዉ ያዩት የተወሳሰበ የተልፈሰፈሰ ችግር ተደማምሮባቸዉ፣ ካርበኞች ግንባርም ሆነ ከኤርትራ መንግስት ጋር መስራት እንደማይቻል ተገንዝበዉ ከቅርብ ጓደኞቻቸዉ ጋር ችግሩን መወያየት የጀመሩትና, ለብቻቸዉ ድርጅት መስርተዉ ለመስራት እንቅስቃሴ የጀመሩት፣ እዚህላይ ችግሩን ለህዝብ ባለማድረሳቸዉ ትልቅ ታሪካዊ ጥፋት አጥፍተዋል።
መታሰብ ያለበት, ያርበኞች የዉጭ ተጠሪ ነኝ, የማእከላዊ ኮሚቴ ነኝ ድርጅታችን ዘመተ ወረደ አሳደደ ወያኔን ደመሰሰ, እያሉ ሲሰብኩ ቆይተዉ, ሳይታሰብ ለብቻ ወጥቶ ሌላ ድርጅት መሰረትን ማለት አገርን ለዉድቀት, ህዝብንም ዉዥንብር ዉስጥ ይከታል፣ የትግልና የፖለቲካ ድርጅት ስነምግባርም አደለም።
ካንድ ድርጅት ጋር ሲሰሩ ቆይቶ ያለመስማማት ቢፈጠር ለብቻ ወይም ከሌላ ድርጅት ጋር ሄዶ መስራት መብቱና ነፃነቱ ነዉ፣ መጀመሪያ ግን እዚያ ድርጅት ጋር ሊቀጥል ያልቻለዉ፣ በምን ምክንያት እንደሆነ ባደባባይ ወጥቶ ማሳወቅ አለበት፡ ወገን እያለቀ አገር እየጠፋ ባለበት ሰአት ያለበቂ ማስረጃ ዘዉ ብሎ ገብቶ ዘሎ መዉጣት አግባብ አይመስለኝም።
የድርጅቱን ችግርና እንቅፋቱን በአደባባይ አጋልጦ እራስን ነፃ አድርጎ ወይም እስካሁን አብሮ ላጠፋዉ ህዝብን ይቅርታ ብላችሁ መልቀቅ ነዉ ያለባችሁ።
በተለይ ያርበኞች ግንባር ችግር ከሁሉም የባሰ ወንድሞቻችን የጠፉበት ገና እየጠፉበትም ያለ ድርጅት ስለሆነ፣ ያን እያወቁ ዘወር ማለት ትልቅ ታሪካዊ ተጠያቂ ያደርጋል፣

ዉድ ወገኖቸ አንባብያን ሆይ፣ እላይ የተጠቀሱትን ሰወች በቅርበት የምታዉቁ ሁሉ እንድትጠይቁልንና እንድታስገድዱልን የምንፈልገዉ,

1ኛ-የተስፋየንና፣ ሺባባዉ አበበ እንዲሁም ሌሎች ብዙ የተገደሉና የጠፉ ሰወችን ሁኔታ, ያርበኞች አመራር ነን የሚሉት በሚዲያ ወጥተዉ እንዲያሳዉቁን ለምኑልን፡
 ሁሉም ኢትዮጵያዊ እላይ ከተጠቀሰዉ ችግር ዉጭ መረጃ ያላችሁ በይፋ አዉጡት፡ የጠፉ የተገደሉ አባሎች የምታዉቁ ሁሉ በይፋ አዉጡት እነዚህን ሰወችም እናፋጥጣቸዋለን፡ ድርጅቱንም ከተቻለ እነዲያገግም ይደረግ፡
2ኛ.ኮ/ል ታደሰን. ሻ/ል ዘዉዱን አቶ ዮሴፍን ባስቸኳይ ስለጤንነታቸዉና ኑሯቸዉ  እንዲያሳዉቁንና ከቁም እስር ወጥተዉ ሁሉም ተረባርቦ ወደ ተሻለ ህይወት የሚመጡበትን መፍትሄ እንዲያስተባብሩ, ሁሉም ኢትዮጵያዊ እንዲረባረብና አገራዊና ሰብአዊ ግዴታዉን እንዲወጣ ድምፁን እንዲያሰማ አደራ እላለሁ።
ቁጥር 3 አላለቀም ቀጣይ አለዉ በሚቀጥላዉ ይጠብቁ። ሰላም ያገናኘን
ላስተያየት፡ ለምስጋና፡ እንዲሁም ወቀሳም ቢሆን ይፃፉልን፡ chakatikur4@gmail.com